በመንግስት በተገነቡ የገበያ ማዕከላት የሚገኙ የንግድ ቤቶችን ለማስተላለፍ እና ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 153/2016

አዲስ አበባ

መመሪያ ቁጥር 153/2016

በመንግስት በተገነቡ የገበያ ማዕከላት የሚገኙ የንግድ ቤቶችን ለማስተላለፍ እና ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ

በአዲስ አበባ ከተማ ተፈጠረውን የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ለመቀነስ እንዲቻል እና በተጨማሪ የገበያ ቦታዎች የሚገኙበት አከባቢና ደረጃቸው ሲታይ ነዋሪዎች ከሚገኙበት አከባቢ የራቀ፤ እንደየንግድ አይነቱ ያልተደራጁ፣ ምቹ ያልሆኑ፤ መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸውና የከተማውን እድገት የማይመጥኑ፤ በመሆናቸው ከተማው አሁን ከደረሰበት እድገት ደረጃ በመነሳት የግብይት ማዕከላትን በመገንባትና ለአምራች፣ ለቸርቻሪ እና ለአገልግሎት ሰጪ ነጋዴ በኪራይ በማስተላለፍ ማዕከላቱ የሚመሩበት ግልፅ አሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህን ችግር ለማስወገድ እንዲቻል አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንደየገበያው የንግድ አይነትና ባህርይ የሰብል ግብይት፣ የቁም እንስሳት፣ የበግና ፍየል፣ የአትክልትና ፍራፍሬና የንግድ አገልግሎት በተለያዩ ቦታዎች በመገንባት ለንግዱ ማህበረሰብ በኪራይ ማስተላለፍና የተገነቡት የገበያ ማዕከላት የሚመሩበት መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 31(13) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በመንግስት በተገነቡ የገበያ ማዕከላት የሚገኙ የንግድ ቤቶችን ለማስተላለፍና ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 153/2016 ተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. "አስተዳደር"ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው።
2. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድ ቢሮ ነው።
3. "የገበያ ማዕከል" ማለት በከተማ አስተዳደሩ የተገነቡ ለሰብል፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ፣ ለቁም እንስሳት፣ ለአገልግሎት መስጫ የሚሆኑ የንግድ ቤቶች ወይም መጋዘን እነ ማከፋፈያ የሚገኙበት ነው።
4. "ነጋዴ" ማለት በገበያ ማዕከሉ በአምራች ወይም በችርቻሮ ወይም በአገልግሎት ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው።
5."የኪራይ ዉል" ማለት ቢሮው ወይም ቢሮው በሚወክለው ድርጅት እና በተከራይ ነጋዴ መካከል የሚደረግ የኪራይ ዉል ነው።
6. "አከራይ" ማለት ቢሮው ወይም ቢሮው የወከለዉ የገበያ ማዕከሉን የሚያከራይ እና የሚያስተዳድር ድርጅት ነዉ።
7.. "ተከራይ" ማለት በከተማ አስተዳደሩ የተገነባውን የገበያ ማዕከል የንግድ ቤት ወይም መጋዘን እና ማከፋፈያ በመከራየት፣ ይህን መመሪያ በቀጣይ የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን አክብሮ በገበያ ማዕከል ዉስጥ ለመነገድ ፈቃደኛ የሆነ ሰዉ ነዉ።
8. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነዉ።
9. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፣

3. የተፈጻሚነት ወሰን፣

ይህ መመሪያ ከከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በመንግስት በተገነቡ የገበያ ማዕከላት፣ የገበያ ማእከላቱን በተከራዩ ሰዎች እና የገበያ ማዕከላቱን በሚያስተዳድረው አካል ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የገበያ ማዕከልን ስለማስተዳደር እና ስለማስተላለፍ

4. የገበያ ማዕከል በኪራይ ስለማስተላለፍ፣

1 በማንኛውም የገበያ ማዕከል የሚገኝ የንግድ ቤት ወይም መጋዘንና ማከፋፈያ ለነጋዴ የሚተላለፈው በኪራይ ነው፡፡

2. የንግድ ቤት ወይም መጋዘንና ማከፋፈያ የሚተላለፈው በቢሮው ወይም ቢሮው በሚወክለው ድርጅት አማካይነት ነው፡፡

3 በገበያ ማዕከሉ የሚገኝ የንግድ ቤት ወይም መጋዘንና ማከፋፈያ በአከራይና በተከራይ መካከል በሚደረግ የኪራይ ውል እና በዚህ መመሪያ መሰረት ይመራል፡፡

4. በገበያ ማዕከል ውስጥ የሚገኝ የንግድ ቤት ወይም መጋዘንና ማከፋፈያ ገበያን ለማረጋጋት እና ተደራሽ ለማድረግ በየትኛውም የአገሪቱ አከባቢ እርሻ ያለው አምራች ግለሰብ፣ ባለሃብት፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች እና የልማት ድርጅቶች ከቸርቻሪ ነጋዴዎች ወይም ከሌሎች ጋር በሚያደርገው ስምምነት በኪራይ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ ከተመለከተው ውጪ በገበያ ማዕከል ውስጥ የንግድ ቤት ወይም መጋዘንና ማከፋፈያ እንዲሁም የአገልግሎት መስጫ የንግድ ቤት መከራየት የሚቻለው በግልጽ ወይም በውስን ጨረታ ላይ ተወዳድሮ አሸናፊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

6. በገበያ ማዕከሉ ውስጥ መጋዘንና ማከፋፈያ እንዲሁም የችርቻሮ መደብር ለመከራየት የሚፈልግ ማንኛውም በየትኛውም የአገሪቱ አከባቢ እርሻ ያለው አምራች ግለሰብ፣ ባለሃብት፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች፣ የልማት ድርጅቶች እና ቸርቻሪ ነጋዴ አከራይ ያወጣውን የጨረታ ማወዳደሪያ መስፈርት ሲያሟላ እንዲሁም የሚያቀርባቸው ምርቶች ዋጋ ቢሮው በሚያቀርበው ሳምንታዊ የምርቶች ዋጋ መነሻነት ቢያንስ ከ15% እስከ 20% ቀንሶ ለመሸጥ ሲስማማ በኪራይ ይተላለፍለታል፡፡

5. የመነገጃ መደብር ወይም ቦታ የኪራይ ድርሻ ድልድል፣

በከተማው የሚስተዋለዉን የገበያ ዋጋ ንረት ለማርገብና የኑሮ ውድነት ለማሻሻል በገበያ ማዕከሉ ተከራይተው የሚነግዱ ነጋዴዎች በተመለከተ በሚከተለዉ ሁኔታ እንደየንግድ ስራ አይነት ባህሪይ ስራ ላይ የሚዉል ይህ ድልድል ወጥቷል፡፡ ይህን ድልድል ቢሮው እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽለው፣ ሊለውጠው ወይም ሊያስቀረው ይችላል፡፡

ተ.ቁ	የንግዱ ዘርፍ	የተከራዩ መለያ	የንግድ ቤት ዓይነት	
			መጋዘንና ማከፋፈያ	መቸርቸሪያ
1	የሰብል ምርት	በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ እርሻ ያለው አምራች ባለሃብት፣ ግለሰብ ወይም ማህበር	✓	
		ለክልል አምራች ህብረት ስራ ዩኒየኖች	✓	
		ለአዲስ አበባ ሸማች የህብረት ስራ ዩኒየን	✓	
		ለአዲስ አበባ ከተማ የእህል ወፍጮ ማህበር		✓
		በእህል ንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ቸርቻሪ ነጋዴዎች		✓
2	አትክልትና ፍራፍሬ	በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ እርሻ ያለው አምራች ባለሃብት፣ ግለሰብ ወይም ማህበር	✓	
		ለክልል አትክልትና ፍራፍሬ አምራች ህብረት ስራ ዩኒየኖች	✓	
		በአትክልትና ፍራፍሬ ችርቻሮ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ነጋዴዎች		✓
3	የቁም እንስሳት	ከብት አድላቢ		
		የእንስሳት ነጋዴ		
4	የአገልግሎት ንግድበገበያ ማዕከላት ውስጥ ለአገልግሎት የተዘጋጁ የንግድ ቤቶች	ግለሰብ ነጋዴ		✓

6. የገበያ ማዕከላቱ የንግድ ስራ ዓይነት መለያ

1. የሰብል የገበያ ማዕከላት
2. የአትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ማዕከላት
3. የቁም እስንሳት የገበያ ማዕከላት
4. የአገልግሎት መስጫ

7. የገበያ ማዕከሉን ስለማስተዳደር፣

የገበያ ማዕከላቱን የሚያስተዳድረው ቢሮው ወይም ቢሮ የሚወክለው ድርጅት ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት

የቢሮው ስልጣንና ተግባር፣ ክፍያ እና የውሉ የቆይታ ጊዜ

8. የቢሮው ሥልጣንና ተግባር፣

1. ቢሮውን ወይም ቢሮው የሚወክላቸው ድርጅት የገበያ ማዕከሉ ዋና ዓላማ የሆነውን የከተማውን ገበያ እና የምርቶችን ዋጋ የማረጋጋት ተልዕኮ በአግባብ እንዲሳካ በሚያስችል አግባብ የገበያ ማዕከሉ ያስተዳድራል፣
2. ቢሮው ወይም ቢሮው የሚወክለው ድርጅት የንግድ ቤቶች፣ መጋዝኖችን እና ማከፋፈያዎችን ያከራያል፣ የኪራይ ውል ይዋዋላል፣ ውል ያቋርጣል፣ የኪራይ ዋጋ ይቀበላል፣ ደረሰኝ ይሰጣል፡፡
3. ቢሮው ወይም ቢሮው የሚወክለው ድርጅት የሚሰበሰበውን ገንዘብ የፋይናንስ ቢሮ ባዘጋጀው የገንዘብ መቀበያ ሰረሰኝ መሰረትበመቀበል በየዕለቱ በንግድ ቢሮ ወይም በፋይናንስ ቢሮ ሂሳብ ደብተር(አካውንት)ገቢ ያደርጋል፣
4. ተከራዮች በሚገቡ ውል መሰረት ግዴታቸውን እንዲወጡ ተገቢውን ጥብቅ ክትትል ያደርጋል፡፡
5. የገበያ ማዕከሉን ሰላምታ ፀጥታ ያከብራል ያስከብራል፣ እንዲሁም ፅዳትና ንፅህና ይጠብቃል ያስጠብቃል፣፡፡
6. በገበያ ማዕከሉን የሚገኙ ተከራዮችን በአግባብ ያስተዳድራል፣ በተከራዮች ማዕከል አለመግባባት ሲፈጠር በገለልተኝነት ችግሩን ይፈታል፡፡
7. የተፈጠረው ችግር ከወኪሉ አቅም በላይ ከሆነ በቢሮ እንዲፈታ ያደርጋል፡፡
8. የገበያ ማዕከሉን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ደህንነት ይጠብቃል፣ የስጠብቃል ይቆጣጠራል፡፡
9. የገበያ ማዕከሉን በአግባቡ ለማስተዳደር የሚያስችል የአሰራር ዘዴ ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይህን መመሪያና የኪራዩ ውል የማያከብር ተከራዮች የኪራዩ ውል ያቋርጣል፣ የቢሮ መብትና ጥቅም ያስከብራል፡፡
10. ከቢሮው የሚሰጠውን የአሰራር መመሪያዎች ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣

11. በአጠቃላይ የገበያ ማዕከሉ የኪራይ ሁኔታ፣ የገንዘብ አሰባሰብ እና የአስተዳደር ሁኔታ ወርሃዊ ሪፖርት ለቢሮ ያቀርባል።

9. የኪራይ ክፍያ

በገበያ ማዕከሉ የሚገኝ የችርቻሮ መደብር ወይም መጋዘን ወይም ማከፋፈያ ተከራይ የኪራዩን ዋጋ በውሉ ይፈፅማል።

10. የቁም እንስሳት የገበያ ማዕከል የአገልግሎት ክፍያ

ወደ ቁም እንስሳት የገበያ ማዕከል እንስሳትን ለገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው በማዕከሉ መግቢያ በር ላይ የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ በወሰነው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይፈፅማል።

11. የተከራይ የኪራይ ቆይታ ጊዜ እና ዉል

1. በሰብል ምርት ላይ የተሠማሩ በየትኛውም የአገሪቱ አከባቢ እርሻ ያለው አምራች ግለሰብ፣ ባለሃብት፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች እና የልማት ድርጅቶች የኪራይ የቆይታ ጊዜ እንደየምርታቸው የሽያጭ ጊዜና ብዛት እየታየ በስምምነት የኪራይ ውል ይደረጋል። ይኸውም እንደየምርታቸው አይነትና የሽያጭ ጊዜ የሚወሰን ይሆናል።
2. በሰብል ምርት ላይ የተሠማሩ በየትኛውም የአገሪቱ አከባቢ እርሻ ያለው አምራች ግለሰብ፣ ባለሃብት፣ የህብረት ስራ ዩኒየኖች እና የልማት ድርጅቶች በስተቀር ማንኛውም ተከራይ በገበያ ማዕከል ውስጥ የተከራይነት ውል ፈርሞ እስከ 1 ዓመት ብቻ መስራት ይችላል። ከ 1 ዓመት በኋላ ውሉ ካልታደሰ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የሚጠበቅበትን ግዴታ ተወጥቶ የተከራየውን የንግድ ቤት ወይም መጋዘንና ማከፋፈያ ለአከራይ አስረክቦ ይወጣል።
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ተከራይ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ማለትም ከሀምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ድረስ የኪራይ ውል ማደስ ግዴታ አለበት። ካልታደሰ ውል ይቋረጣል።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም በአከራይና በተከራይ መካከል በሚደረገው የኪራይ ውል ላይ ውሉን ማቋረጥ የፈለገ ወገን በቅድሚያ የ1 ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ማቋረጥ ይችላል፡፡

ክፍል አራት

የገበያ ማዕከሉ አከራይ፣ ተከራይ መብትና ግዴታዎች

12. የተከራይ መብት

1. በገበያ ማዕከል ዉስጥ በኪራይ ውል መሰረት በተረከቡት ንግድ ቤት፣ መጋዘንና ማከፋፈያ በተፈቀደለት ወይም በንግድ ሥራ ፈቃዱ መሠረት የመነገድ መብት አለው፣
2. በገበያ ማዕከሉ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን መብራት(ጄኔቴተር) ማጥም የመፀዳጃ ቤት፣ ውሃ፣ ከሌሎች ተከራዮች ጋር በጋራ መጠቀም መብት አለው፣
3. በቢሮው የተወከሉ ድርጅት በአሠራርም ሆነ በሚወሰደው ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ የሚኖርን አለመግባባት እና ቅሬታ ለቢሮው ማቅረብ ይችላል፡፡

13. የተከራይ ግዴታ፣

1. በዚህ ውል አንቀጽ 9 ላይ በተመለከተው መሠረት በየወሩ የንግድ ቤት፣ መጋዘንና ማከፋፈያ ኪራይ ዋጋ እና በማዕከሉ መግቢያ በር ላይ የአገልግሎት ክፍያ መክፍል አለበት፡፡

2. ተከራይ ቤቱን በመሉም ሆነ በከፊል በኪራይም ሆነ በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም፡፡

3. ተከራይ የኪራይ ውል ጊዜ ሲያበቃ የተከራየውን የንግድ ቤት፣ መጋዘንና ማከፋፈያ በተረከበት ሁኔታ ለአከራይ መልሶ የማስረከብ ግዴታ አለበት፣
4. ተከራይ ቤቱን የሚጠቀመው በማዕከሉ ለተፈቀደ ለንግድ ሥራ አገልግሎት ብቻ ነው፡፡
5. ተከራየውን ንግድ ቤት፣ መጋዘን ወይም ማከፋፈያ ከነበረበት ውጪ መለወጥ፣ ማሻሻል ምንም ዓይነት ግንባታ መጨመር አይችልም የንግድ ቤትን መጋዘንና ማከፋፈያ ጣሪያ ወለል ግድግዳ መብሳት የተከለከለ ነው፣

6. ለተገለገለበት የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የስልክ፣ የጥበቃና የፅዳት አገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡
7. የማዕከሉን መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የማዕከሉን የጋራ መገልገያዎች ከሌሎች ተከራዮች ጋር በጋራ መጠቀም፣
8. ማንኛውም ተከራይ በተከራየው ንግድ ቤት፣ መጋዘን ወይም ማከፋፊያ ላይ ሆን ተብሎም ሆነ በቸለተኝነት ለሚደርስ የአያያዝ ጉድለት ወይም ብልሽት በተከራዩ ወጪ የማስተካከል ወይም የማሠራት ግዴታ አለበት፣ ነገር ግን ብልሽቱ ያጋጠመው ከግንባታ ጉድለት ወይም በእርጅና ምክንያት ከሆነ የማስተካከል ኃላፊነት የአከራይ ይሆናል፡፡
9. በቁም እንስሳት የገበያ ማዕከል በእንስሳት ንግድ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በአንቀጽ 10 ላይ በተመለከተው መሠረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፣
10. ወደ ገበያ ማእከሉ ገብተው የሚሰሩ አምራቾችም ሆነ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ለሽያጭ የሚቀርቡት የምርት ዋጋ ከገበያ ማዕከላቱ ውጪ ከሚካሄደው የጅምላና የችርቻሮ የገበያ ዋጋ ቢያንስ ከ15% እስከ 20% መቀነስ አለባቸው፡፡
11. ማንኛውም ነጋዴ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 10 በፐርሰንት የተጠቀሰውን ቀንሶ የመሸጥ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ቅናሽ የገበያ ዋጋ ያላከበረ ማንኛውም ተከራይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የኪራይ ውሉ ተቋርጦ የገበያ ማዕከሉን ለቆ ይወጣል፡፡

14. የአከራይ መብት

1. አከራይ በዚህ ውል መሠረት ለአከራይ ባከራየው የንግድ ቤት፣ መጋዘን ማከፋፊያ ላይ የባለቤትነት ወይም የባለንብረትነት መብት አለው፡፡
2. አከራይ በህግ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ራሱ ወይም በወከለው ድርጅት አማካኝነት የገበያ ማዕከሉን አሰራር፣ ይዞታውን የማስተዳደርና የመቆጣጠር መብት አለው፡፡
3. አከራይ በዚህ ውል አንቀጽ 9 ላይ በተጠቀሰው መሰረት የንግድ ቤቱን የመጋዘኑ እና የማከፋፊያው የኪራይ ዋጋ በየወሩ ከተከራይ ላይ የመቀበል እንዲሁም በቁም እንስሳት የገበያ ማዕከል በሚገለገሉ ነጋዴዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ላይ በተመለከተው መሰረት የአገልግሎት ክፍያ የመቀበል መብት አለው፡፡

15. የአከራይ ግዴታ

1. በሚወክለው ድርጅት እና በተከራዮች መሀከል ለሚፈጠር አለመግባባት መፍትሄ ወይም መልስ መስጠት አለበት፣
2. የገበያ ማዕከሉን ሕንፃ፣ አጥር፣ የኤሌክትሪክ ማመንጫ(ጄኔሬተር) የውሃ ታንከር ደህንነት ወይም አገልግሎት አሠጣጥ መከታተልና ለሥራ ዝግጁ ማድረግ አለበት፣

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ

16. ቢሮው የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጆዎች

ቢሮው ይህን መመሪያ ተላልፎ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፣

1. በገበያ ማዕከሉ ውስጥ ፈቃድ ሳያሳድስ በውሉ መሰረት ኪራይ ሳይከፍል፣ የሚደረስበት ነጋዴ ላይ የንግድ መደብሩን ወይም መጋዘኑን ወይም ማከፋፈያውን ያሽጋል፣
2. ነጋዴው የገበያ ማዕከሉን ንጽህ ከጓደለ ወይም ሰላምና ፀጥታ ካወከ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣
3. ለሽያጭ የሚቀርበው ምርት ዋጋ ከገበያ ማዕከላት ወጪ ካለው ዋጋ ንግድ ቢሮ በየሳምንቱ በጥናት እየለየ ከሚያቀርበው የገበያ ዋጋ ከ15% እስከ 20% ቀንሶ ካልሸጠ የኪራይ ውሉን ያቋርጣል፣
4. ተከራይ የተከራየውን ለ3ኛ ወገን ካስተላለፈ ውሉን ያቋርጣል፣ ባለንብረቱ ንብረቱን እንዲያወጣ በማድረግ የንግድ ቤቱን ያሽጋል፣ ይረከባል፣

17. ውክልና ስለመስጠት

ቢሮው ይህን መመሪያ ለማስፈፀም ለ3ኛ ወገን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

18. የተሻሩ ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያም ሆነ ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

19. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በቢሮው ሊሻሻል ይችላል፡፡

20. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው እና በራሱ በፍትሕ ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ቢኒያም ምክሩ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ

መጋቢት 16 ቀን 2016ዓ.ም